የስራና ክህሎት ዘርፍ የሙስና ሥጋት ግምገማዊ ጥናት

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION
1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ግንቦት/ 2015

አዲስ አበባ

ማውጫ

ክፍል አንድ: መግቢያ 3
1.1. የጥናቱ ዳራ (Background of the study) 3
1.2. የዘርፉ አጠቃላይ ገጽታ 4
1.3. የጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study) 5
1.3.1. አጠቃላይ ዓላማ፡- 5
1.3.2. ንዑስ አላማዎች፡- 5
1.4. የዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ጥናት ጠቀሜታው 5
ክፍል ሁለት 6
ስራ እና ክህሎት ዘርፍ የሙስና ስጋት የተዛማጅ ጹሁፎች ዳሰሳ 6
2.1. በዘርፉ አለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ተጨባጭ ሁኔታ የተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ 7
2.2. ለሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ሊዳርጉ የሚችሉ የአሰራር ክፍተቶች 8
ክፍል ሶስት፡ የጥናቱ ስነ ዘዴ 9
3.1. የጥናቱ ቦታ 9
3.2. የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች 9
3.3. ጥናቱ የተከናወነበት ሂደት 10
3.4. የሙስና ስጋት ጥናት ስነ-ዘዴ 10
3.5. የጥናቱ ዓይነት እና የመረጃ ትንተና ዘዴ 11
3.6. የጥናቱ ተግዳሮቶች 11
ክፍል አራት፡-ዘርፍ-ተኮር የሙስና ሥጋት ትንተና 11
4.1. የተቋማት አደረጃጀት 11
4.2. ተጠያቂነትን ማስፈን 13
4.3. የተቋማት ግልጽነት ትንተና 14
4.4. አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ 15
4.5. ንብረት አስተዳደር 16
4.6. የግዥ አስተዳደር 16
4.7. የሰው ሀብት አስተዳደር 17
4.8. ሀብት ማሳወቅና ምዝገባ 18
4.9. የፕሮጀክት አስተዳደር 19
4.10 የኦዲት እና ቁጥጥር ሥርዓት 19
4.11. የሙስና ስጋት 20
ክፍል አምስት፡ ምክረ ሃሳቦች 21
ማጣቀሻ 24
አባሪ ሀ፡ የስራ እና ክህሎት ዘርፍ የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና 25

ክፍል አንድ: መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ (Background of the study)

ሙስና በሀገራት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተፅዕኖ በብዙ በተለያየ መንገድ የሚገለፅ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ በፖለቲካ፤ በኢኮኖሚ፤ በማህበራዊ፤ በተፈጥሮ ሀብቶችና አካባቢ ጥበቃ፤ በሠላም እጦትና አለመረጋጋት፤ በህግ የበላይነት መሸርሸር፤ በሰው ልጆች መሠረታዊ የሠብአዊ መብቶችና ነፃነቶች መጣስ፤ የዜጎች የፍትሀዊ ሀብት አጠቃቀምና ተመጣጣኝ የመልማት መብትን ከማሳጣት ባለፈ የመልካም አስተዳደር አለመኖርንና የዜጎች መብቶች እንዳይከበሩ በማድረግ ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳል።

በዚህ ችግር ከተጠቁ የአለማችን አህጉሮች ውስጥ አህጉራችን አፍሪካ ግንባር ቀደም ስትሆን ሀገራችን ኢትዮጵያም የዚህ ችግር ሠለባ ከሆኑት የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ ትጠቀሳለች። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመታገል ተቋም ከማቋቋም የተለያዩ እንቅስቃሴ ስታደርግ ቆይታለች፤ እያደረገችም ትገኛለች።

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አብይ ተልዕኮ ከሆኑት መካከል በተቋማት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ክፍተት የሚፈጥሩ አሰራሮችን በጥናት መለየትና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ማመላከት ነው። በዚሁ መሰረት በተያዘው በጀት አመት ዘርፍ ተኮር አሰራርን በመከተል በ19 ዘርፎች ስር የሚገኙ ተቋማት የስራ አፈፃፀምና የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት ለማካሄድ የሚያስችሉ መረጃዎችን በመሰብሰብ እና በመተንተን በተገኙ ግኝቶች ላይ የመፍትሄ ሀሳቦችን መስጠት የሚያስችል ጥናት እያካሄደ ነው።

በተቋማት ለሙስና ስጋት እንደመነሻ ይሆናሉ ተብለው የሚታሰቡ ሁኔታዎችን ማለትም የህጎች ክፍተትና መላላት፣ የቁጥጥር ማነስ፣ ደካማ የአስተዳደር ሥርዓት፣ ደካማ ተቋማዊ ባህል፣ ደካማ የአሰራር ስርዓት፣ የግለሰቦች የሥነምግባር ጉድለት፣ የሥራ አካባቢዎች አለመመቸት እና አግባብነት የሌላቸው የሥራ ግንኙነቶች፣ የግልፅነትና ተጠያቂነት አሰራር አለመኖር፣ የጥቆማ አቀራረብ፣ አያያዝ እና አፈታት ግልፅነት አለመኖር፣ የመረጃ አያያዝ ደካማነት ተጠቃሽ ናቸው።

ዘርፉ የፌደራል አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሠረት የተቋቋመ እና በስሩ የሚገኙት ተቋማትም ለዚሁ ዘርፍ ተጠሪ እንዲሆኑ ተደርገው በአዋጁ የተደራጁ ናቸው።

የእነዚሁ ተቋማት ዋና ዋና ተልዕኮዎች በአገሪቱ ያለውን የስራ አጥነት ችግር ለመፍታት የሚያስችል ወጥነት እና ዘላቂነት ያለው ስርዓት መዘርጋት፣ ዜጎች ክህሎታቸው ዳብሮ በሚሰሩባቸው የስራ ዘርፎች ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን ሙያዊ፣ ስነልቦናዊና አካላዊ ብቃት እንዲገነቡ ማድረግ፣ የቴክኒክና

ሙያ ስልጠና ልማት፣ የቴክክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የማስፈፀም አቅምን መገንባት እና ውጤታማ የምርምር ስራዎችን በማካሄድ ውጤት ተኮር የስልጠና ስርዓትን መደገፍ፣ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሰልጠና ዘርፍ በተሻለ ደረጃ ላይ ከሚገኙ የውጭ ሀገር ተቋማት ጋር የትብብር ግንኙነት፤ ለቴክክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ጠቃሚ የሆኑ ምርምርና ጥናቶችን በማካሄድ ውጤቶችን ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣ በሆቴልና ቱሪዝም መስክ የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ለሃገራችን የሆቴልና ቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዕድገት ማበርከት ነው፡፡

በመሆኑም ይህ የጥናት ሪፖርት ከዚህ በታች በተመለከተው ዘርፍና ተቋማት ላይ በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ የሚያተኩር ሲሆን በ11 የጥናት ርዕሰ ጉዳዮች መሰረት ለተገኙ የሙስና ስጋቶች መፍትሔ ኃሳቦችን የሚያመለክት ሲሆን በዘርፉ ከሚገኙ አራት ተቋማት የኢትዮጵያ ኢንተርፕርነርሽፕ ልማት ኢኒስቲትዩት በአዲስ መልክ የተቋቋመ እና ገና በመደራጀት ላይ ያለ በመሆኑ ጥናቱ ትኩረት ባደረገባቸው 10 ነጥቦች ላይ መረጃ ባለመኖሩ ይህ ትንተና በተቀሩት ሶስት ተቋማት በተሰበሰቡ መረጃ ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡

1.2. የዘርፉ አጠቃላይ ገጽታ

ዘርፉ በስሩ ሶስት ተጠሪ ተቋማት የሚገኙበት ሲሆን የፌደራል መንግሥት የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ 1263/2014 መሰረት የተቋቋሙ ሲሆኑ በአጠቃላይ የዘርፉ ዋና ዓላማ ቀደም ሲል ተባታትነው በስራ እድል ፈጠራ፣ በክህሎት፣ በኢንዱስትሪ ሰላምና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ይሰሩ የነበሩ ተቋማትን ወደ አንድ በማምጣት እያስተባበሩ ለመስራት ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠርና የስራ አጥነት ችግር ለመፍታት የሚችል ወጥነት እና ዘላቂነት ያለው ስርዓት መዘርጋት ዜጎች ክህሎታቸው ዳብሮ በሚሰሩባቸው ዘርፎች ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን ሙያዊ፣ ስነልቦናዊና አካላዊ ብቃት እንዲገነቡ የማድረግ ተልዕኮን የያዘ ሲሆን ዘርፉ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ልማት፣ ማኔጅመንትና ቁጥጥር ተግባራትን ማከናወን፣ የሥራ እድል ፈጠራ፣ ስራና ሰራተኛ ስምሪት አገልግሎቶችን ማስፋፋት፣ ማስተባበርና መምራት፣ የኢንዱስትሪ ሰላም ማስጠበቅ፣ ለውጭ ሀገራት ዜጎች የስራ ፈቃድ በመስጠት የእውቀት፣ ክህሎትና ቴክኖሎጅ ሽግግርን ማፋጠን፣ ህገወጥ የሰዎችን ዝውውር መከላከል፣ ዓለም ዓቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የቴክኒክና ሙያ መምህራንና ቴክኒሽያኖችን እንዲሁም የአመራር አካላትን በቅድመ ምረቃና በድህረ ምረቃ እንዲሁም ሌሎች አጫጭር ስልጠናዎች በመስጠት ማብቃት፤ የቴክክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የማስፈፀም አቅምን መገንባት፤ የሀገሪቱን ኢንዱስትሪ በተለይም የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን ምርታማነት እና ተወዳዳሪነት የሚያጎለብት የቴክኖሎጂ ሽግግር መደገፍ እና ውጤታማ የምርምር ስራዎችን በማካሄድ ውጤት ተኮር የስልጠና ስርዓትን መደገፍ ነው፡፡

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋሞች ለተሰማሩ ባለሙያዎች በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ የንድፈ ሃሳብና የተግባር ስልጠና መስጠት፣ ጥራቱን የጠበቀ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት የሚያግዙ አጫጭር ስልጠናዎችና የምርምር አገልግሎት መስጠት፣ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ በተሻለ ደረጃ ላይ ከሚገኙ የውጭ ሀገር ተቋማት ጋር የትብብር ግንኙነት መመስረት፣ አግባብነት ላላቸው የክልል ተቋማት የቴክኒክ እገዛና ምክር መስጠት፣ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ጠቃሚ የሆኑ ምርምርና ጥናቶችን በማካሄድ ውጤቶችን ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣ በሆቴልና ቱሪዝም መስክ የሰለጠነ የሰው ሃይል ፍላጎት ማሟላት እና ኢንዱስትሪው ላይ ያሉትን ሙያተኞች የማብቃት፤ የጥናትና ምርምር ማካሄድና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራትን ማከናወን ነው፡፡ በዚህ ጥናት የተካተቱ የዘርፉ የፌደራል ተቋማት ብዛት አራት ሲሆኑ እነሱም፡ የኤፌዲሪ ስራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢኒስቲትዩት፣ ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢኒስቲትዩት እና የኢንተርፕርነርሽፕ ልማት ኢኒስቲትዩት ናቸው፡፡

1.3. የጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study)

1.3.1. አጠቃላይ ዓላማ፡-

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በስራና ክህሎት ዘርፍ ሥር በሚገኙ ተቋማት ዘርፍ ተኮር የሙስና ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት ማካሄድ ነው፡፡

1.3.2. ንዑስ አላማዎች፡-

የዚህ ጥናት ንዑስ ዓላማዎች በስራና ክህሎት ዘርፍ ሥር በሚገኙ ተቋማት፥ 1) የአሠራር ስርዓትን / የስራ አፈፃፀምን መገምገም፤2) የሙስና ተጋላጭነትን ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፤3) ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ ሃሳቦችን ማስቀመጥ፣

1.4. የዘርፍ ተኮር የሙስና ስጋት ጥናት ጠቀሜታው

የሙስና ትርጉም:1) በኦክስፎርድ ዲክሽነሪ፡- አደራን አለመጠበቅ፣ እምነት ማጉደል፣ በጉቦ፣ በምልጃና በአድሎ፣ ሐቅን፣ ውሳኔን ወይም ፍትህን ማዛባት፡፡ 2) በካቶ (1996)፡- ለግል ወይም ለቡድን ጥቅም ሲባል፣ ሥርዓቶችን፣ ደንቦችን፣ ህጐችንና መርሆዎችን መጣስ ነው፡፡ 3)የሙስና ቅኝት በኢትዮጵያ 1993:- የመንግስትን ሥራ ሥነ ምግባራዊና ህጋዊ መሠረት ባለው መመሪያና ደንብ ላይ ተመርኩዞ አለመስራት፡፡ 4)Transparency International:- በመንግስትና በህዝብ የተሰጠን ሥልጣንና ኃላፊነት ለግል ጥቅም፣ ወይም ሌላን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲባል በስልጣን አለአግባብ መገልገል ነው፡፡ ሙስና ህግና ሥርዓትን ተከትሎ ከመስራት ይልቅ ስልጣንና ኃላፊነትን መከታ በማድረግ ህግና ሥርዓትን በመጣስ

የመንግስትና የህዝብ ሃብትና ንብረትን መስረቅ፣ መዝረፍ፣ ማጭበርበር እንዲሁም በጉቦ፣ በዝምድና፣ በትውውቅ በጉስኝነት፣ በፖለቲካ ወገንተኝነትና በኃይማኖት ትሥሥር በመመርኮዝ ፍትህን እያዛቡ የግል ጥቅምን ማካበትና ሌላውን ወገን ተገቢ ባልሆነ መንገድ መጥቀም ወይም መጉዳት ነው፡፡

ግለሰቦች ወደ መንግስት ሃላፊነት በሚመጡበት ጊዜ የተሰጣቸውን ሃላፊነት በህግና በአግባብ እንዲጠቀሙበት ቢጠበቅም ይህንን ሃላፊነት ለግል ጥቅም ማካበቻ የሚያውሉበት ሁኔታ ካለ ሙስና ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ሙስና የግል ጥቅምን ለማግኘት በሚል ሃላፊነትን ባግባቡ አለመጠቀም ወይንም ሃላፊነትን ተጠቅሞ ያልተገባ ነገር ማድረግን ይመለከታል፡፡ ሃላፊነትን ለግል ጥቅም ማዋል በሚለው እይታ ውስጥ በርካታ ተግባራት ሊዘረዘሩ ይችላሉ፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የሙስና ወንጀልን ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 881/2015) 25 የሙስና ወንጀል ተግባራት በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ የዚህ የሙስና ስጋት ጥናት ዋና ጠቀሜታው፡- ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ተከስተዉ ከፍተኛ ጉዳት ከማድረሳቸዉ በፊት ለችግሩ ክፍተት የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መርምሮ በማዉጣት የመፍትሄ ሀሳቦችን በማቅረብ ችግሮች ከወዲሁ እንዲቀረፉ ለማድረግ ያስችላል፤ ይህንን ጥናት ስፖንሰር ያደረገው የፌዴራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እስከሆነ ድረስ ኮሚሽኑ በራሱ መንገድ ለፖሊሲ ግብአት ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለቀጣይ ከሙስና ጋር በተያያዘ ለሚደረጉ ጥናቶች እንደ ማጣቀሻ ሰነድ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

ክፍል ሁለት

ስራ እና ክህሎት ዘርፍ የሙስና ስጋት የተዛማጅ ጹሁፎች ዳሰሳ

ሙስና ለልማትና እድገት ጸር የሆነ ዓለም አቀፋዊ ክስተት ነው። ሙስና የሚፈጸምበት ደረጃ ከአገር አገር የተለያየ ቢሆንም ሙስና የማይፈጸምበት አገር አለ ማለት አይቻልም። ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት (Rent-seeking) ከድህነት ለማላቀቅና ጠንካራ የኢኮኖሚ መሰረት ለመገንባት የሚደረግ ትግልን በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዳ ተግባር ነው። በዓለማችን ሙስናን በከፍተኛ ደረጃ ከቀነሱ ሀገሮች መካከል ዴንማርክ፣ ኒውዚላንድና ሲንጋፖር ሲሆኑ ነገር ግን ሀገራቱ ከሙስና ሙሉ በሙሉ የጸዱ እንዳልሆኑ ጥናቶች ያሳያሉ። ሙስናን ትርጉም ባለው መልክ መቀነስ አገራት ለሚያራምዱት ልማት መሳካት ወሳኝ እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ። የመንግሥት ባለሥልጣናት ሥልጣናቸውን አላግባብ በመጠቀም መምራት በተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል። የህዝብ ሀብት መዝረፍ፣ የማጭበርበር፣ የይገባኛል ጥያቄዎች እና በቀጥታ የጉቦ ደረሰኞችን ጨምሮ በህብረተሰቡ ወጪ ከፍተኛ የግል ጥቅማጥቅሞችን በማቅረብ በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል (Blackburn et al.፣ 2011)። ሙስና እና ስራ አጥነት ብዙ የአፍሪካ ታዳጊ ኢኮኖሚዎችን የሚያጋጥሟቸው በጣም አንገብጋቢ የፖሊሲ ጉዳዮች ናቸው።

በአፍሪካ ሀገራት ያለው ከፍተኛ ሙስና የመንግስትን ኢንቨስትመንት ጥራት በመቀነስ የግል ካፒታል ኢንቨስትመንትን ያዳክማል። በዚህም ምክንያት ደካማ እድገትን ያስከትላል ይህም ቀጣይነት ያለው ሥራ አጥነት፣ የኢኮኖሚ አለመረጋጋትን እና ሕገወጥ የሆኑ ድርጊቶችን በጥቂር ገበያ መልክ እንዲጨምር ያደርጋል(Ndikumana (2006)፣ Bakare 2011)።

2.1. በዘርፉ አለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ተጨባጭ ሁኔታ የተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ

የቅጥር አገልግሎት መስጠት የስራ ገበያ ፖሊሲዎችና ደንቦች ቁልፍ ተግባር ነው። በዚህ ብቻ ባይወሰንም፣ የሥራ ስምሪት አገልግሎት ዋና ዓላማ ከአሰሪዎችና ከሥራ ፈላጊዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ማዛመድ ነው። በዚህ ሴክተር ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና አደጋዎችን የምንረዳበት በርካታ መንገዶች አሉ። በዘርፉ ላይ የተመሰረቱ የሙስና አደጋዎች በፖሊሲ አወጣጥ ደረጃ ያልተገባ ተጽእኖ፣ በሰራተኞች ቅጥር አሰራር ላይ ዘመድ ወዳድነት፣ በክህሎት ማሰልጠኛ ወይም የስራ ማእከል ውስጥ በደንበኛ መስተጋብር ጉቦ እና ከግዢ ጋር የተያያዘ ማጭበርበር ይገኙበታል። እነዚህን ስጋቶች ለመቅረፍ የስራ ገበያን በትክክለኛ መተንተን፣ ኦዲት ማድረግ እና ቤንችማርክ ማስቀመጥ፣ የቁጥጥር ዘዴዎችን ውጤታማነት ማረጋገጥ እና አካታች አስተዳደርን ለማስፋፋት በማህበራዊ ንግግሮች ላይ ትኩረት ማድረግን ጨምሮ በርካታ የሆኑ ዘዴዎች መኖራቸውን ጥናቶች ያሳያሉ።

በተለያዩ የስልጠና ኮርሶች የከፍተኛ ሰራተኞችን ክህሎት ማሳደግ፣ የጀማሪ ሰራተኞችን እድገትን ሊጨምር ይችላል። በደቡብ አፍሪካ በሁሉም ዘርፎች የለውጥ እና የኢኮኖሚ ዕድገት ቁልፍ ፈተና እንደሆነ በሰፊው የሚታወቅ የክህሎት ቀውስ ገጥሟታል (Plant and Padotan 2017፣ ቸልቸሌ 2009)፣ ደቡብ አፍሪካ አሁንም እንደ ልማታዊ መንግሥት የምትቆጠር በመሆኗ በአገሪቱ ያለው የክህሎት እጥረት አንዱና ዋነኛው እንቅፋት እንደሆነ ጠቁመዋል። ስለዚህ በመንግስት ሴክተር ውስጥ ያሉ ክህሎትን ማዳበር በተለይ የመንግስት ሴክተር ሰራተኞች የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል እና የህይወትን ጥራት ለማሻሻል የሚረዱ ፕሮግራሞችን ለመቅረጽ እና ለመተግበር ሙያዊ እውቀት ስለሚያስፈልጋቸው ነው (Kroukamp 2002፣ Qwabe and Pillay 2009፣ በማፉኒሳ 2014)።

አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በመንግስት ዘርፍ ያለው ከፍተኛ ደመወዝ ከዝቅተኛ ሙስና ጋር ግንኙነት አለው (Van Rijckegem and Weder 2001, An and Kweon 2017)። እንዲሁም በመንግስት ሴክተር ዝቅተኛ የሆነ ደሞዝ ከፍተኛ ሙስና ያስከትላል (Panizza 2001, Ades and DiTella 1997, and Treisman 2000 2007፣ Rose-Ackerman and Søreide, 2012)።

የሰራተኛ ደረጃን ለማበረታታት የቁጥጥር መስፈርቶች በአንድ ገበያ ውስጥ ተግባራዊ እና ተጨባጭ መሆን አለባቸው ሲሉ ይከራከራሉ (በካን፣ አንድሮኒ እና ሮይ፣ 2016)፡፡ በአንዳንድ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ድርጅቶች ደንቦችን የማክበር አቅም ላይኖራቸው ይችላል፡፡ ጥናቱ እንደሚያመላክተው በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ኩባንያዎች የሠራተኛ ተቆጣጣሪዎችን ወደ ሌላ መንገድ እንዲመለከቱ በመክፈል ወይም የቅጥር አገልግሎት አቅራቢዎችን ለህገወጥ አቅርቦት ሠራተኞች ጉቦ በመስጠት እንደ ኢኮኖሚያዊ ሕልውና ብልሹ አሠራር ውስጥ እንደሚሳተፉ ይጠቁማል፡፡ በደንብ ያልተነደፉ የስራ ገበያ ደቦች ለሙስና እና ለኪራይ ሰብሳቢነት ባህሪ እንደ መፈልፈያ ቦታ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ ምክንያቱም በህግ መስፈርቶች እና በኢኮኖሚው እውነታ መካከል ባለው የማይታለፍ ክፍተት ምክንያት ጨዋነት የጎደላቸው ባለስልጣናት ህጎቹን ማክበር ካልቻሉ ድርጅቶች ጋር ህገወጥ ድርድር ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ አጠቃላይ ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት (Rent-seeking) ከእደገት እንቅፋቶች መካከል ቀዳሚነት ስፍራ ይይዛል፡፡ የህዝብን ደህንነትና የተረጋጋ ኑሮን ያናጋል፡፡ መልካም አስተዳደር እንዳይሰፍን ያደርጋል፡፡ የወደፊት ተስፋን ያጨልማል፤ የአገራትን የመልማት እቅድ ያሰናክላል፡፡

2.2. ለሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ሊዳርጉ የሚችሉ የአሰራር ክፍተቶች

በተለያዩ ደረጃዎች ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን የሚያበረታቱ በርካታ ምክንያቶች አሉ እነሱም 1) አውዳዊ ሁኔታዎች (ከስራ ስምሪት አገልግሎት ኤጀንሲ ቁጥጥር ውጪ የሆኑ ነገሮች)፡- የተወሰኑ የአደጋ ምክንያቶች የስራ ገበያዎችን እና የቅጥር ኤጀንሲዎችን የሚቆጣጠር ግልጽ ያልሆነ ወይም ወጥነት የሌለው ህግ፣ ሙስናን ለመከላከል እና ታማኝነትን ለማጠናከር የሚያስፈልጉ መሰረታዊ የህግ ማዕቀፎች (እንደ የስነ ምግባር ደንቦች፣ የጥቅም ግጭት ህጎች፣ የህዝብ መረጃ ህጎችን በነፃ የማግኘት መብት፣ የንብረት መግለጫ ህጎች፣ የስነምግባር ህጎች፣ የሎቢ ህግ እና የጠላፊዎች ጥበቃ)፣ ውጤታማ ያልሆነ ህግ አስከባሪ እና ክስ፣ ብቃት የሌላቸው የቁጥጥር ተቋማት ወይም ተቆጣጣሪ ባለስልጣናት፣ ግልጽ ያልሆኑ የህዝብ ፋይናንስ ሂደቶች፣ ደካማ የሆነ የመንግስት ሴክተር አሠራር እና የተሳሳተ ግንዛቤ፣

2) ድርጅታዊ ሁኔታዎች (በድርጅቱ ወይም በሴክተሩ ቁጥጥር ስር ያሉ ሁኔታዎች፣ የመልካም አስተዳደር ደንቦች እና ፖሊሲዎች፣ የአስተዳደር፣ የውሳኔ አሰጣጥ፣ የአሠራር መመሪያ እና ሌሎች የውስጥ መመሪያዎች)፡- ደካማ ስልታዊ እና ተግባራዊ መመሪያዎች ወይም በቂ ያልሆኑ ፖሊሲዎች፣ ሂደቶች ወይም ስርዓቶች፣ ነባር ፖሊሲዎችን፣ አካሄዶችን ወይም ሥርዓቶችን መከተል፣ ሥር የሰደደ ውድቀት፣ ግልጽ ያልሆነ የቅጥር ኤጀንሲ ስልጣን፣ ደካማ ወይም ወጥነት የሌላቸው የውስጥ ድርጊቶች እና ደንቦች፣ የተለያዩ አይነት ብልሽቶች ሲኖሩ የማስተካከያ እና የማስጠንቀቂያ አሰራር ስርዓቶች አለመኖር፣ ሙስናን ለመከላከል ዙሪያ ያለው ደካማ የአመራር እና አስተዳደራዊ እርምጃዎች፣ በቂ ያልሆነ/ደካማ የስራ

ግምገማ፣ ክትትል፣ ቁጥጥር እና የኦዲት ዘዴዎች፣ የስነምግባር ባህሪን እና ግልጽነትን የሚያበረታቱ ህጎች እና ሂደቶች አለመኖር፣ የበላይ ኃላፊዎችን እና ተቆጣጣሪዎችን ጨምሮ የመንግስት ባለስልጣናት በቂ ያልሆነ የስልጠና እና የትምህርት ስርዓት፣ በቂ ያልሆነ የሰው፣ የገንዘብ እና የጊዜ ሀብት ::

3) ግለሰባዊ ሁኔታዎች (ግለሰቦችን ወደ ብልሹ ወይም ሥነ ምግባር የጎደለው ድርጊት እንዲፈጽሙ የሚያነሳሱ ምክንያቶች)፡- የሚፈለገው እውቀት ማነስ፣ ታማኝነት ማጣት፣ የተግባር ክህሎቶች እጥረት፣ በሥራ አካባቢ ውስጥ ያሉ ጫናዎች፣ በቂ ያልሆነ ቁጥጥር ወይም የአፈጻጸም ግምገማ፣ ከደንበኞች ጋር ተገቢ ያልሆነ ግንኙነት፣ የጥቅም ግጭት መግለጫዎችን መተው፣ የስራ እርካታ ማጣት ወይም ኢፍትሃዊ ግንዛቤዎች፣ 4) የሥራ ሂደት ሁኔታዎች (በድርጅት ውስጥ ካለው የሥራ ሂደቶች የሚነሱ ምክንያቶች)፡- ከፍተኛ የግል አስተሳሰብ፣ ግልጽ ያልሆነ ወይም ያልተቀዳ የውሳኔ አሰጣጥ፣ ደካማ የሥራ ሂደቶች አደረጃጀት፣ ያልተገናኘ የስራ ሂደት እና የአሰራር ክፍተቶች፣

ክፍል ሶስት፡ የጥናቱ ስነ ዘዴ

3.1. የጥናቱ ቦታ

ይህ የዘርፍ ጥናት የተካሄደው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገኙ በፌደራል የክህሎትና ስራ ፈጠራ ሚኒስቴር እና የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተጠሪ በሆኑ 3 (ሶስት) ተቋማት (በኤፌዲሪ ስራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ በፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢኒስቲትዩት፣ በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢኒስቲትዩት እና የኢንተርፕርነርሽፕ ልማት ኢኒስቲትዩት ላይ ነው፡፡

3.2. የመረጃ ምንጮች እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህ ጥናት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች በመጠይቅ እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች (brainstorming) ናቸው፡፡ ከየተቋማቱ የተሰበሰቡ የተለያዩ ሰነዶች ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

መጠይቅ፡- የጥናት ቡድን አካላት የተቋማት የተለያዩ የሥራ ክፍል ኃላፊዎችንና ሰራተኞችን በማወያየት እንዲሁም (እንዳስፈሊጊነቱ) በምልከታ የተዘጋጀውን ቼክ-ሊስት እንዲሞላ ተደርጓል፡፡ ጥናቱን ከሌሎች ጥናቶች ለየት የሚያደርገው በቼክ-ሉስት ላይ የተነሱ ነጥቦች አዎንታዊ ምላሽ የሚሰጣቸው በሰነድ ወይም በምልከታ ሲረጋገጡ ብቻ መሆኑ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የሙስና ግንዛቤ (perception) ጥናት ሳይሆን በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሰረተ የተቋማት የስራ አፈፃፀም እና የሙስና ተጋላጭነት ጥናት ነው፡፡

ሰነዶች፡- የተቋማቱ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች፣ የውስጥና የውጪ ኦዲት ሪፖርቶች፣ ዓመታዊ በጀት ዕቅድ፣ የግዥ አፈጻጸም፣ ዓመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች፣ የሙስና መከላከል ሠነዶች፣ የጥቆማ ሪፖርት አያያዝ፣ አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ሪፖርቶች፣ ወዘተ ተዳሰዋል።

የሃሳብ ማጎልበቻ ዉይይት፡- እንደሚታወቀው የሙስና ስጋቶች ከአንድ ተቋም ወደ ሌላ ተቋም የመለያየት ባሕሪ አላቸው። ስለሆነም ተቋም-ተኮር የሙስና ስጋት ልየታ ለማካሄድ በጥናቱ በተካተቱ ተቋማት ውስጥ የበርካታ አመታት ዕውቀት ካላቸው በጥንቃቄ ከተመረጡ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች (experts) ጋር ኃሳብ የማጎልበት ውይይት ተካሂዷል።

3.3. ጥናቱ የተከናወነበት ሂደት

ይህን ጥናት ለማከናወን በአማካሪዎች፣ በጥናት ቡድን መሪዎችና በመረጃ ሰብሳቢዎች አማካኝነት ሶስት ዋና ዋና ሂደቶችን የተከተለ ሲሆን አንደኛው የጥናቱ መጠይቅ ዝግጅት ሲሆን መጠይቁን ለማዘጋጀት የተለያዩ አለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ተሞክሮወችን እና ተያያዥ ጽሁፎችን በመዳሰስ ለማዘጋጀት ተችሏል። በዚህ ምዕራፍ ከተከናወኑ ተግባራት መካከል፡- የተዘጋጀውን መጠይቅ የሚመለከታቸው አካላት እንዲወያዩበት እና እንዲፀድቅ ተደርጓል፣ ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ለጥናት ቡድን መሪዎች የስልጠና ሞጁል በማዘጋጀት ስልጠና የተሰጠ ሲሆን በሁለተኛው ምዕራፍ የመረጃ መሰብሰብ ሂደት ሲሆን የመረጃው አሰባሰብ ሂደት በሁለት ዓይነት ዘዴ የተዘጋጀ ሲሆን 1ኛ) በሃርድ ኮፒ እና 2ኛ) በሶፍት ኮፒ የተቋማት መረጃ ተሰብስቧል። የመረጃዉን ተአማኒነት ለማረጋገጥ ሁሉም መጠይቆች መረጃ ከተሞላባቸዉ በኋላ ከተሰበሰበው የሰነድ ማስረጃ ጋር እንዲረጋገጥ ተደርጓል። በተጨማሪም መረጃው ተሰብስቦ ካለቀ በኋላ ርክክብ ከመፈፀሙ በፊት የመረካከቢያ ፎርም በማዘጋጀት ያልተሟሉ መረጃዎች እንዲሟሉ ተደርጓል። በመረጃ ስብሰባ ወቅት ተገቢ የሆኑ የስነ-ምግባር መርሆችን በመከተል፡- የግለሰቦችንም ሆነ የተቋምን መብት የማይጋፋ እና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ እንዲሁም የመረጃዉን ሚስጥራዊነት እንዲጠበቅ ተደርጓል። የሶስተኛው ሂደት የሪፖርት ዝግጅት ሲሆን በዚህ ምዕራፍ ከተከናወኑ ተግባራት መካከል ስለ ሪፖርት አጻጻፍ ለጥናት ቡድን መሪዎች እና አባላት ስልጠና ተሰጥቷል፣ በስልጠናው መሰረት የተዘጋጀውን ረቂቅ ሪፖርት ቀርቦ የሚመለከታቸው አካላት እነዲወያዩበት እና እንዲፀድቅ ተደርጓል።

3.4. የሙስና ስጋት ጥናት ስነ-ዘዴ

የተለያዩ የዓይነታዊ የመረጃ ትንተና ስልቶች መካከል አንዱ የሆነውን ቲማቲክ (ጭብጥ ተኮር) የምርምር ዘዴ የተጠቀምን ሲሆን ይህ የጥናት ዘዴ በመረጃ ውስጥ ፓተርንን (ርዕስን) የመለየት፣ የመተንተን እና ሪፖርት የማድረግ ዘዴ ነው። አብዛኛውን ጊዜ የመረጃውን መጠን የሚቀንስ ገላጭ የሆነ የትንተና ዘዴ ነው። ይህ አካሄድ የተለያዩ ዘዴዎችን ሊያካትት ይችላል። አብዛኛውን ጊዜ የዳሰሳ ጥናት መጠይቆች፣

የቡድን ውይይቶች እና በተለያዩ የጽሑፍ ስብስቦች ላይ ይተገበራል። ጭብጥ ትንተና ዘዴን በመጠቀም ተመራማሪው በጽሁፎቹ ውስጥ በተገለጹት ርእሶች እና ሃሳቦች ላይ ተደጋጋሚ ንድፎችን ወይም ጭብጦችን ለመለየት የመረጃ ስብስብ ያጠናል። የዓይነታዊ መረጃዎችን በመተንተን፣ የቲማቲክ (ጭብጥ ተኮር) ትንተና በፅንሰ-ሀሳቦች፣ አስተያየቶች እና ልምዶች ላይ ያተኩራል። ይህ ውስብስብ፣ ገላጭ እና በተለያዩ ፍልስፍናዊ እና ፅንሰ-ሀሳባዊ መሠረቶች ላይ ሊጣበቅ የሚችል የመረጃ አቀራረብን የሚጠይቅ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የሙስና ስጋት ደረጃን ለመተንተን የአሀዛዊ መረጃ የትንተና ዘዴ የሆነውን የሙስና ስጋት ማትሪክስ ጥቅም ላይ ውሏል።

3.5. የጥናቱ ዓይነት እና የመረጃ ትንተና ዘዴ

የዚህ ጥናት አቀራረብ በአብዛኛው ዓይነታዊ (qualitative) ነው። ገላጭ ትንተና (descriptive analysis) አሀዛዊ መረጃዎችን (የፕሮጀክቶች የወጪ መረጃና አፈፃፀም፣ የግዥ አፈፃፀም 4 ማሳያዎች፣ የውጭ እና የውስጥ የኦዲት ሪፖርት ግኝቶች፣ ወዘተ) በመተንተን ሥራ ላይ ውሏል። ከተለያዩ ምንጮች (መጠይቅ፣ ሰነዶች እና የሀሳብ ማጎልበቻ ውይይቶች) የተሰበሰቡ ዓይነታዊ መረጃዎችን ለመተንተን ይህ ጥናት በሰፊው ተቀባይነት ያለውን የጭብጥ ትንተና (thematic analysis) ዘዴ ተጠቅሟል።

3.6. የጥናቱ ተግዳሮቶች

ይህ ጥናት የተለያዩ ተግዳሮቶች ያጋጠሙት ሲሆን እነሱም፦ የተቋማት ኃላፊዎች/ ሰራተኞች በተያዘላቸው ቀጠሮ ያለመገኘትና ጥናቱን የሚያከናውኑትን ባለሞያዎች የማመላለስ፣ የተቋማት ኃላፊዎች መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፣ በተለይም የኦዲት ግኝት እና የፕሮጀክት መረጃዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን ወይም በሚፈለገው ጊዜ አለመስጠት፣

ክፍል አራት፡-ዘርፍ-ተኮር የሙስና ሥጋት ትንተና

የስራና ክህሎት ዘርፍ የሙስና ስጋት ትንተና በ11 ርዕሰ-ጉዳዮች ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል።

4.1. የተቋማት አደረጃጀት

በዘርፉ ስር ከሚገኙት ተቋማት ውስጥ ስራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢኒስቲትዩት፣ ቱሪዝም ማሰልጠና ኢኒስትቲዩት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት አቋቁመዋል። የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስትትዩት ሁሉም መደቦች በሰው ኃይል የተሟላ ሲሆን በስራና ክህሎት ሚኒስቴር አንድ ስራ

አስፈጻሚ በቋሚነት አንድ ባለሙያ እንዲሁም በቱሪዝም ማስልጠኛ ኢንስትትዩት አንድ የስነ ምግባር ስራ አስፈጻሚና አንድ ባለሙያ ያላቸው ሲሆን ሌሎች የስራ መደቦች ክፍት መሆናቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በጀትን በሚመለከት እንደሌሎች የስራ ክፍልች የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን በሚጠይቁበት ወቅት የሚፈቀደበት አሰራር (ፑል ሲስተም) ሁሉም የዘርፉ ተቋማት እየተተገበሩ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዘርፉ በሁሉም ተቋማት ውስጥ የሚገኙ የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል የሚያስፈልጉ የቢሮ ቁሳቁሶች ማሟላታቸውን እና የ2015 በጀት አመታዊ ዕቅድ አቅደው እየተንቀሳቀሱ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የሀብት ብክነትንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተፈጠሩ አደረጃጀቶች መኖራቸውን በተመለከተ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፤ የዲሲፒሊን ኮሚቴ፣ የግዢ አፅዳቂ ኮሚቴ፣ የደረጃ እድገት ኮሚቴ፣ ወዘተ የተቋቋሙ መሆናቸውን ለማየት ተችሏል፡፡

ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበል የሚያስችል ሚስጥራዊነቱን የጠበቀ ዘዴ ተብሎ ሊጠቀስ የሚችልው በአካል በመገኘት ጥቆማ የሚሰጥበት የጥቆማ መስጫ ሳጥን፣ ኢ-ሜይል፣ ድረ-ገጽ እና ስልክ የመሳሰሉት በዘርፉ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት ተደራሽ ተደረገው እየተተገበሩ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዘርፍ ስር ከሚገኙት ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸው ከሌሎች ክፍሎች (ከህግ ክፍሉ፣ ተቋማዊ ለውጥ፣ ውስጥ ኦዲት፣ ወዘተ) ጋር በቅንጅት የሚሰሩ መሆኑን መረጃዎች አመላክተዋል፡፡

በዘርፉ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት ውስጥ ውጫዊ እና ውስጣዊ ውሎች ከመፈረማቸው በፊት የህግ ክፍሎች አስተያየት የሚሰጡበት አሠራር ስርዓት ስለመኖሩ መረጃዎች ማግኘት አልተቻለም፡፡ አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት ስለመኖሩ የሚያሳዩ መረጃዎች ማግኘት አልተቻለም፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ከላይ የተገለፁት ጉዳዩች በዘርፉ ስር ከሚገኙት የሥነምግባር መከታተያ ክፍልች ከፌደራል ቴክኒክና ሙያ በስተቀር የተስጣቸውን ተልዕኮ ለመወጣት የሚያስችል የተሟላ አደረጃጀት የሌላቸው መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

በስራና ክህሎት ዘርፍ የተቋማት አደረጃጀትን በተሟላ ሁኔታ አለማደራጀትን ተከትሎ ሊፈጠሩ የሚችሉ የሙስና ስጋቶች መካከል የስነምግባር መከታተያ ክፍል በተሟላ ሁኔታ አለመደራጀቱ፣ እራሱን የቻለ የበጀት አመዳደብ ያለመኖር፣ ውጫዊ እና ውስጣዊ ውሎች ከመፈረማቸው በፊት የህግ ክፍሎች አስተያየት የሚሰጡበት አሠራር ስርዓት ስለመኖሩ፣ ለሚከናወኑ የስነምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል ተግባር ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

4.2. ተጠያቂነትን ማስፈን

ተቋማት የዜጎችን ፍትህ ለማረጋገጥ፤ አስተዳደራዊ በደሎችን ለማረምና ለመቀነስ፣ የመንግስት በጀትና ሃብት በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውል የዜጎች ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ለማስቻል እንዲሁም የዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክሲያዊ መብቶች እንዲጠበቁ፤ በስነ ምግባር የታነፀ፣ ሙስናንና ብልሹ አስራሮችን የሚፀየፍ ዜጋን ለማፍራት ተቋማቶች ተጠያቂነት ማስፈን አስፈላጊ ነው፡፡ ተጠያቂነት አንድ ግለሰብ ወይም ተቋም ከተሰጠው ስልጣንና ከተጣለበት ኃላፊነት ጋር በተያያዘ አፈፃፀሙን በመገምገም ለሚፈጠሩ ጥፋቶች ኃላፊነት ማረጋገጥ ይገባል፡፡

በዚህ ረገድ በዘርፍ ስር የሚገኙ ሶስት ተቋማት ማለትም በስራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ በፌደራል ሙያና ቴክኒክ ማስልጠኛ ኢንስትትዩት እና ቱሪዝም ማስልጠኛ ኢንስትትዩት ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎችን የዳሰሳ ጥናት መደረጉን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ሆኖም የሙስና ስጋት ዳሰሳዊ ጥናቱን ተከትሎ የታዩ ማሻሻያዎችን የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ በተጨማሪም የደንበኞች እርካታ ጥናትን በተመለከተ በዘርፉ ስር በሚገኙ በሁሉም ተቋማት በገለልተኛ አካል ጥናት ስለመደረጉ መረጃ አልተገኘም፡፡ ይህ አለመደረጉ ዘርፉ ከተጠያቂነት አንጻር ሲታይ ክፍተት ያለበት መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ ተጠያቂነት ለማስፈን ከሚያስችል ተግባራት መካከል የሥነምግባር ደንብ (Code of conduct) ማዘጋጀትና መተግበር አንዱ ተግባር ነው፡፡ ይህን ኃላፊነት ከመወጣት አንፃር በዘርፉ ስር የሚገኙ ሶስቱም ተቋማት የሥነ-ምግባር ደንብ (Code of conduct) ማዘጋጀታቸውን ከሰነድ ማስረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት ቅድመ የመከላከል ስራዎች በሚመለከት በዘርፉ ስር ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ በፌደራል የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስትቲዩት ከትምህርት ዕድል ጋር በተያያዘ አንድ ጥቆማ ቀርቦ በተደረገው የቅድመ መከላከል ስራ የእርምት እርምጃ መወሰዱን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ ስር ከሚገኙ ተቋማት በሁለት ተቋማት ማለትም በፌደራል ቴክኒክና ሙያ ማስልጠኛ እና በቱሪዝም ማስልጠኛ ውስጥ በስነምግባር ጉድለት ምክንያት አንድ አመራርና አምስት ፈጻሚ በድምሩ ሰባት የቀረቡ ክሶች እንዳሉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም አብዛኛዎቹ ክሶች በሚባል ደረጃ ውሳኔ የተሰጣቸው ሲሆን ከውሳኔዎቹም መካከል ሁለት ባለሙያዎች ከስራ እንዲሰናበቱ እና አንድ ባለሙያ በይቅርታ እንዲመለስ የተደረገ መሆኑንና ሌሎች ወደ ፍርድ ቤት ያመሩ መሆናቸውን ከመረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዘርፉ ስር በሚገኙ አራት ተቋማት መካከል በሁለቱ ተቋማት ማለትም በፌደራል ቴክኒክና ሙያ ማስልጠኛ እና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስትዩት በድምሩ ዘጠኝ (9) ክሶች የህግ ክፍሉ የፍትሐብሔርና የወንጀል ክሶች

የመሰረቱ ሲሆን በሁለት ክሶች (22.2%) የረቱ መሆኑን መረጃዎች የሚያስገነዝቡ ሲሆን ቀሪ ሰባት ክሶች በሂደት ላይ እንደሚገኙ መረጃዎች አመላክተዋል፡፡

የቅሬታ አቀራረብ ስርዓትን በተመለከተ በዘርፉ በርካታ ጉዳዮች ላይ በሥራና ክህሎት፣ በቱሪዝምና በፌደራል ሙያና ቴክኒክ ማስልጠኛ ኢንስቲትዩት ባለፉት ሁለት ዓመታት ቅሬታዎች እንደቀረቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እነዚህ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በተቋማቱ ባለፉት ሁለት ዓመታት 178 ቅሬታዎች ቀርበው ሁሉም ውሳኔ አግኝተዋል፡፡ ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት እንደተቻለው የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ክፍል የስራ አፈጻጸም በተቋማቱ የበላይ ኃላፊዎች ይገመገማል፡፡

ተጠያቂነትን ከማስፈን ማነስ የሚመነጩ የሙስና ስጋቶች መካከል የደንበኞች እርካታ ጥናትን በተመለከተ በዘርፉ ስር በሚገኙ በሁሉም ተቋማት በገለልተኛ አካል ጥናት አለመደረጉ እንደስጋት የሚወሰድ ነው፡፡

4.3. የተቋማት ግልጽነት ትንተና

ተቋማት የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ለተገልጋዮችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ግልፅነት ያለውን አሰራር መከተል እና ተገልጋዮችን አሳታፊ ማድረግ ሙስናን ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችል ይሆናል፡፡ በዘርፉ የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስትቲዩት እና የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ተቋማዊ ግልፅነት ለማሰፈን እንዲያግዝ የተለያዩ ስራዎች መሰራታቸውን ከቀረበው መረጃ እና መስክ ምልከታ መረዳት ተችሏል፡፡

በሁሉም ተቋማት እቅዶችና ሪፖርቶች በየደረጃው የኮር ማኔጅሜንት ካውንስል አባላትና ባለድርሻ አካላት/ ተጠሪ ተቋማትና ክልሎች/ በሚገኙበት መድረክ በጋራ በየ3 ወር ውይይት እንደሚደረግበት ከቀረበው መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተቋማቱ የሚካሄዱ የእቅድ አፈጻፀም ግምገማዎች ሪፖርቶች ብልሹ አሰራሮችን ለመለየት ማስቻላቸውን ከሪፖርት ግምገማ መረዳት ተችሏል፡፡ አመታዊ መደበኛ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ ከማድረግ አኳያ የስራና ክህሎት ሚኒስቴር እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች እንዲውቁት እንደሚደረግ ከሰነድ እና ከገለፃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በዘርፉ ባሉ ሁለት ተቋማት የእቅድ አፈፃፀም ግምገማዎች በየደረጃው ከተካሄዱና ክፍተቶች ከተለዩ በኋላ ሪፖርቱ ማጠቃለያ ላይ የተቋሙ የበላይ ሃላፊዎች አቅጣጫና አስተያየት የሚሰጡበት ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የመከታተያ ስርዓት የተዘረጋለት ሲሆን በተቋሙ ያሉ የስራ ሂደቶች ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚመለከታቸውን አካላት እና የማኔጅመንት አባላት የሚሳተፉ መሆኑን ከቀረበው መረጃ ለመረዳት

ተችሏል፡፡ የግዢ ጨረታ ማስታወቂያዎችን በይፋ ማሰራጨትን በተመለከተ በዘርፉ ካሉ ተቋማት ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር እና ፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢኒስትቲዩት በድረገፅ፣ በጋዜጣ እና በቴሌቪዥን በመጠቀም ተደራሽ እንደሚያደርጉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

4.4. አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ

ሙስናን መዋጋት ከሚያስችል ጉዳዮች መካከል አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡፡ የህግ የበላይነት ከማስፍን ባሻገር ተግባራዊ ማድረግ ያለባቸው መርሆች በመደንገግ ፈፃሚዎች ስራቸውን ህግ በተከተለ መንገድ እንዲሰሩ አስገዳጅ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ክትትል ከማድረግ በተጨማሪ በየጊዜው መሻሻል ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስትቲዩት፤ የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት እና የሥራ ክህሎት ሚኒስቴር በጥናት ስራዎች ከሚመነጩ መረጃዎች በመነሳት አዳዲስ ህጎች የማውጣትና ነባር ህጎችን የማሻሻል ስራ እየተሰራ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለምሳሌ የነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ፤ የመደበኛ ስልክ አጠቃቀም መመሪያ፤ የኤክስቴንሽን መርሃግብር የትርፍ ሰዓት መመሪያ ፤የፋይናንስ ግልጽነትና ተደራሽነት መመሪያ፤ የስነ ምግባር መመሪያ፤ የመኖሪያ ቤት አስተዳደር መመሪያ፤ የሴኔት ሊጂስሌሽን መመሪያ፤ የደንብ ልብስና ደህንነት መመሪያ ፤የስርዓተ ጾታ ማካተቻ ስልጠና፤ የሙስና የስጋት መመሪያ የትምህርት እድል ፈጠራ፤የሬጅስትራር ጽ/ቤት መመሪያ፤ እና ሌሎች መመሪያዎች የጾታ ስጋት መከላከል መረጃ፤ የማህበረሰብ አገልግሎት መመሪያ እና ሌሎች የሥነ-ምግባር ደንቦችና ሙስና መከላከል የሚያስችል መመሪያዎች በማውጣት ተግባራዊ እያደረጉ መሆናቸው ከቀረቡ ሰነዶች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በዘርፉ ከ40 በላይ አዋጅ፣ ደንቦችና መመሪያዎች የወጡ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 30 መመሪያዎች መሆናቸውን መገንዘብ የተቻለ ሲሆን ሁሉም የዘርፉ ተቋማት በሚወጡ መመሪያዎችና ደንቦች ላይ ለተቋሙ አመራሮች እና ሰራተኞች ስልጠና እንደሚሰጡም ከመረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ ፀድቀው የሚወጡ መመሪያዎችና ደንቦች ለተገልጋዮች/ለደንበኞች በቀላል ተደራሽ በማድረግ ረገድ በቴሌግራም ቻናል፣ በዌብሳይት፣ በድረገፅ፣ በኢንስቲትዩሽናል ኤሜይል እና ሌሎች ዲጅታል አማራጮችን በመጠቀም ተደራሽ የሚያደርጉበት አሰራር እንዳለ ከተቋሙ ከህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን እንዲሁም ICT ስራ ክፍሎች በምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የዜጎች ቻርተርን በተመለከተ የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትት እና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ ማድረጋቸውን ለማየት ተችሏል፡፡

4.5. ንብረት አስተዳደር

በዘርፉ ስር የሚገኙ ሶስት ተቋማት ንብረትን ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር የሚጠቀሙበት Integrated Financial Management Instrument Sytem/IFMIS/ እና Financial Management Instrument Sytem/FMIS/ ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ስርዓቱን ከሚጠቀሙ ባለሙያዎች ማየትና መረዳት የተቻለ ሲሆን ስርዓቱም በትክክል የሚሰራ መሆኑን በአካል ምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የንብረት ቆጠራ ሪፖርትን በሚመለከት የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲቲዩት እና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት አመታዊ የንብረት ቆጠራ ያካሄዱ ሲሆን የስራና ክህሎት ሚኒስቴር ቆጠራ አለማካሄዱን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የካይዘን ንብረት አስተዳደር ስርዓትን በሚመለከት ከላይ በበጎ የተገለፁት ተቋማት ስርዓቱን የሚተገብሩ ሲሆን ሌሎች ቀሪ ሁለት ተቋማት የካይዘን ንብረት አስተዳደር ሥርዓትን ተግባራዊ እንደማያደርጉ ከተሰበሰበው መረጃና ከሲስተም ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የተወገዱ ንብረቶችን በተመለከተ የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትት እና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ጊዜ ያለፈባቸውን ንብረቶች ዝርዝር በማቅረብ በባለሙያዎች አስገምግመው በእርዳታ መልክ ያስወገዱ መሆኑን መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ ለሚወገዱ ንብረቶች ተገቢውን ጥበቃና አያያዝ ከማድረግ አንፃር ንብረት የማስወገድ ስራ ያከናወኑ ተቋማት ንብረቶችን በአንድ ቦታ ላይ በማከማቸት ጥበቃ እንደሚደረግላቸው ከመጋዘን (store) በተደረገ ምልከታ መረዳት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ የዘርፉን የንብረት አስተዳደር ስርዓት ስንመለከት ሁለት ተቋማት ጥሩ አፈፃፀም ያሳዩ ሲሆን የስራና ክህሎት ሚኒስተር የንብረት ቆጠራ፣ አያያዝና፤ ጥበቃና አወጋገድ ሂደትን የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ ነገር ግን የንብረት አወጋገድ ስርዓትን ተግባራዊ ባለማድረጋቸው ዘርፉ ለሙስና ሥጋት የተጋለጠ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

ከንብረት አሰተዳደር ስርአትና አፈፃፀም አኳያ በዘርፉ የንብረት አወጋገድ ስርዓት ተግባራዊ አለመደረጉ አሰራሩ ለሙስና ሥጋት የተጋለጠ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

4.6. የግዥ አስተዳደር

የዘርፉን የግዥ አፈፃፀም ሂደት በሚመለከት የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲቲዩት እና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲቲዩት የግዥ እቅድ እንዳላቸውና የእቅድ ግምገማ አድርገው ግዥ እንደሚፈፅሙ እንዲሁም የግዥ አፈጻጸማቸውን እንሚገመግሙ ከተሰበሰበው መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ነገር ግን የስራና ክህሎት ሚኒስቴር የግዥ እቅድ ባለመኖሩ ያከናወኑት የዕቅድም ሆነ የአፈፃጸም ግምገማ የለም፡፡

የዘርፉን የግዥ አፈፃፀም ማሳያዎችን በሚመለከት የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምሀርትና ስልጠና ኢንስቲቲዩት ያለ እቅድ፤ በፐርፎርማ፣ በውስን ጨረታ እና በተደጋጋሚ ከአንድ አቅራቢ ግዥ ያከናወነ

መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የተለያዩ ግዥዎችን ቢያከናውንም በየትኛው የግዥ መንገድ እንደፈፀመ የሚያሳይ መረጃ የለም፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በሁለቱም ተቋማት ቅሬታ የቀረበበትም ሆነ በሙስና የተጠረጠረ ብሎም የተሰረዘ ግዥ ስለመኖሩ የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ የስራና ክህሎት ሚኒስቴር ምንም አይነት የስራ እቅድና በጀት የሌለው መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡
የግዥ ሂደትን ለማከናወን እነዚሁ ተቋማት ሰቶክ ላይ ያላቸውን እቃ ተመርኩዘው ግዥ እንደሚፈፅሙ ከተሰበሰቡ የሰነድ ማስረጃዎች ማየት የተቻለ ሲሆን ስራና ክህሎት ሚኒስቴር ስቶክ ላይ ተመስርተው ስለመፈፀማቸው የሚያሳይ ማስረጃ አልተገኘም፡፡ ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ግዥ ከመፈፀሙ በፊት ቅድመ ገበያ ጥናት አድርጎ ግዥ መፈፀሙን ከተሰበሰበው የጥናት ሪፖርት መረዳት የተቻለ ሲሆን ቀሪዎቹ ተቋማት በዚህ ጉዳይ አለማከናወናቸውን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ዲጂታላይዝድ የግዥ አሰራር ሥርዓትን ከመተግበር አንፃር ሁሉም የዘርፉ ተቋማት ሲስተሙን የዘረጉ ቢሆንም ወደ ተግባር የገቡት ግን የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት እና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ሲሆኑ የስራና ክህሎት ሚኒስተር ሲስተሙን ቢዘረጋም ሥርዓቱን ተጠቅሞ ግዥ ስለመፈፀሙ የሚያሳይ መረጃ የለም፡፡

የዘርፉ ተቋማት ግዥ ስርዓትና አፈፃፀም በተመለከተ ሊጠቀሱ ከሚችሉ የሙስና ስጋቶች መካከል በዕቅዱን መሰረት አድርጎ ግዥ አለመፈጸም፣ የግዥ ዕቅድ አፈፃጸም ግምገማ አለመደረጉ፤ ያለ እቅድ፤ በፐርፎርማ፣ በውስን ጨረታ እና በተደጋጋሚ ከአንድ አቅራቢ ግዥ ማከናወን፤ ተቋማት ግዥ ሲፈፀም በተሟላ ሁኔታ ስቶክ ላይ ባለው በመመስረት አለመፈጸሙ በማንኛውም ዓይነት የመንግስት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት በማሰብ ግዥ ሊከናወን ይችላል፡፡

4.7. የሰው ሀብት አስተዳደር

በዘርፉ በስራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት እና የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የሰራተኛ አስተዳደር ክፍል የቅጥር፣ የዲስፒሊን፣ የቅሬታና ደረጃ እድገት ኮሚቴዎች መቋቋማቸውን ከቀረበ መረጃ ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን በኢንተርፐርነርሺፕ ልማት ኢንስቲትዩት የቅጥር ኮሚቴ ብቻ ያለው መሆኑን ከቀረበ ደብዳቤ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የቅጥር ማስታወቂያዎችን ተደራሽ ማድረግን በተመለከተ በሶስት ተቋማት ስራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት እና የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲቲዩት በጋዜጣ፣ በድህረግፅ እና የውስጥ ማስታወቂያ ሰሌዳ በመጠቀም ተደራሽ ማድረጋቸውን ከቀረበ መረጃ ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን የኢንተርፕረነርሽፕ ልማት ኢንስቲትዩት ግን "ኢትዮ ጆፕ" በሚባል በኦን ላይን ስርዓት ማስታወቂያ በማውጣት የቅጥር ሂደቱንም በዚያው እንደሚያካሂዱ በምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከሰራተኛ ቅጥር ጋር የተያያዘ አንድ ቅሬታ እንዲሁም ከደረጃ እድገት ጋር ሁለት ቅሬታዎች መቅረባቸውንና ሁሉም ቅሬታዎች መፍትሔ ያገኙ መሆኑን ከቀረበ መረጃ ማጣራት የተቻለ ሲሆን በስራና ክህሎት ሚኒስቴር ከጂኤጂ መዋቅር ጥናት ምደባ ጋር በተያያዘ 167 ቅሬታዎች የቀረቡ መሆናቸውንና ለ55 ጉዳዮች መፍትሔ የተሰጠ መሆኑ 112 ቅሬታዎች አላግባብ የቀረቡ ቅሬታዎች መሆናቸው ከተደረገ ማጣራት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በሌላ መልኩ የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት የቀረበ ቅሬታ አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዘርፉ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ እና የስራ ልምድ የማጣራት ስራ ስለመሰረቱን የሚገልፅ መረጃ የለም፡፡

የአመራር ምደባዎች በተመለከተ በዘርፉ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት በግልጽ መስፈርት ማለትም የስራ ማስታወቂያ በቦርድ እና በጋዜጣ ላይ እንዲወጣ በማድረግ የሚቀጠርበት ሁኔታ እንዳለ ከቃለ ጉባኤ እና ሌሎች ደጋፊ ሰነዶች ለመረዳት ተችሏል፡፡ የሰው ሀብት መረጃን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ማደራጀትን በተመለከተ በሥራ ክህሎት ሚኒስቴር ስራው ገና በሂደት ላይ ሲሆን በፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲቲዩት በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የተዘጋጀ ዘመናዊ የሰው ሀብት መረጃ ስርዓት /ISMIS/ እየተጠቀሙ እንደሆነ፣ የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ቴክኖሎጂን መጠቀማቸውን የሚያመላክት መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡

ስራና ክህሎት ሚኒስቴር እና የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት በፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 በሚመለከት፣ በቅሬታ አቀራረብ፣ የሞራል እሴት ግንባታ ላይ ድግግሞሽን ጨምሮ ለ1,515 አመራርና ባለሙያዎች ስልጠና መስጠቱን ከመረጃዎች ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲቲዩት የሙያ ብቃት ስልጠና ስለመስጠቱ የሚያመላክት መረጃ አልተገኘም፡፡

ከሰው ሀብት አስተዳደር አኳያ በዘርፉ የሰው ሀብት የስራ ክፍል የሀሰተኛ የትምህርትና የሥራ ልምድ መረጃን የማጣራት ስራ አለመሰራቱ ማንኛውም ሰው የራሱንም ሆነ የሌላውን መብትና ጥቅም ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሊያገኝ ይችላል፡፡ የስራ እና ክህሎት ዘርፍ መንግስታዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሃሰት መለወጥ ወይም በሀሰተኛ ሰነድ መገልገል የሙስና ወንጀል ስጋት ያለበት መሆኑን ጥናቱ ያመላክታል፡፡

4.8. ሀብት ማሳወቅና ምዝገባ

በዘርፉ በአጠቃላይ ሀብት ማስመዝገብ የሚገባቸው 132 አመራር እና 1247 ሰራተኞች በድምሩ 1,379 ሲሆኑ ከዚህ ውስጥ ያስመዘገቡ 62 አመራሮች እና 543 ሰራተኞች በድምሩ 605 መሆናቸውን መረጃዎች

አመላክተዋል፡፡ ስራ እና ክህሎት ሚኒስቴር እና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢኒስትቲዩት በህጉ በተቀመጠው የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስርዓት መሰረት እንዳላስመዘገቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ ሥርዓት የግል እና የመንግስት ጥቅም ሳይጋጩ ተጠያቂነትን ባሰፈነ መልኩ ለመተግበር እና የጥቅም ግጭቶችን ለመከላከል እና ምንጫቸው ያልታወቀ (ተገቢ ያልሆኑ) ንብረቶችን ለመለየት ካለው ፋይዳ አንፃር በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት በተሟላ ሁኔታ አለመከናወኑ እንደስጋት ምንጭ ሊወሰድ ይችላል፡፡

4.9. የፕሮጀክት አስተዳደር

ፕሮጀክት ከሚያንቀሳቅሰው ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ፣ ከሚጠይቀው የሰው ኃይልና ካለው ልዩ ባህሪይ አንጻር ለሙስናና ብልሹ አሠራር ያለው ተጋላጭነት ከፍተኛ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በዘርፉ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ የፕሮጀክቶቹ አፈፃፀምን በተመለከተ በቀረበው መረጃ መሰረት በፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲቲዩት ተጀምሮ በጊዜው ያላለቀ አንድ ፕሮጀክት በገንዘብ 279,395,828.06 ብር እና ተጨማሪ ሥራ የተሰጠበት አንድ ፕሮጀክት በገንዘብ 9,178,979.15 ብር መሆኑን የተሰበሰበው መረጃ የሚያሳይ ሲሆን በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የዋጋ ግምቱ 1.6 ሚሊየን ብር የሆነ አንድ ፕሮጀክት በጊዜው ያላለቀ መሆኑን ከቀረበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የዋጋ ማስተካከያ የተደረገባቸው፣ ተጨማሪ ሥራ የተሰጠባቸው እና ያለ በጀት የተጀመሩ ፕሮጀክቶች አፈጻፀም የሚያሳይ መረጃ ስለመኖሩ መረጃ አልቀረበም፡፡

በስራና ክህሎት ዘርፍ ከፕሮጀክቶች አፈጻጸም ጉድለት አኳያ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ስጋቶች፦ ተገቢውን መረጃ አደራጅቶ አለመያዝ፣ ግልጽ አለመሆን፣ ሙስናንና ብልሹ አሠራርን መከላከል የሚያስችል የአሠራር ስርዓት አለመዘርጋታቸው እንደሙስና ስጋት ሊታይ ይችላል፡፡

4.10 የኦዲት እና ቁጥጥር ሥርዓት

በዘርፉ ስር የተደራጁ ተቋማት የተቋቋሙበትን ዓላማ በትክክል እያሳኩ እና የተመደበላቸውን ሀብት በቁጠባና በውጤታማነት መጠቀማቸውን በኦዲት ማረጋገጡ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በዘርፉ ስር የሚገኙ እነዚህ ሶስቱ ተቋማት የውስጥ እና የውጭ ኦዲት ሪፖርት በሚመለከት ያሉበትን አፈጻፀም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስትቲዩት እና የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የውስጥ ኦዲት ሪፖርት መደረጉን መረጃዎች የሚያመላክቱ ሲሆን በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በውስጥ ኦዲት በተገኘ ግኝት መሰረት 28,523,043.49 ብር ያልተወራረደ መሆኑን የቀረበው ሰነድ ሲያሳይ የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስትቲዩት የውጭ የኦዲት ግኝቶችን የሚያመላክት መረጃ የለም፡፡

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የ2014 ዓ.ም በጀት ዓመት የውጭ ኦዲት ሪፖርት የቀረበ ሲሆን የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ግን ማግኘት አልተቻለም፡፡ በኦዲት ግኝቱ ላይ የተቀመጡ አስተያየቶችን በመተግበር ለዋና ኦዲተርና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት ማድረግ የኦዲት ተደራጊው ግዴታ ቢሆንም በዘርፉ የሚገኙ ተቋማት ይህን ማድረጋቸው የሚያሳይ መረጃ የለም፡፡ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በውስጥ ኦዲት ግኝቶችን ለማሻሻል ለሚመለከተው የሥራ ክፍል ተደራሽ ማድረጉ እንደ ጥሩ ጅምር ሊወሰድ ይችላል፡፡ በዘርፉ የሚገኙ ተቋማት የኦዲት ሪፖርቶችን ተመስርተው ማሻሻያዎች ስለማድረጋቸው በተጨባጭ የሚያሳይ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በዘርፉ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት በሁሉም ተቋማት በወቅቱ የውስጥና የውጭ ኦዲት በማድረግ ረገድ ውስንነት እንዳለ፣ የተሟላ የኦዲት ሪፖርት አለመስጠታቸው፣ የቀረቡ የማሻሻያ ሃሳቦች ተግባራዊ ማድረጋቸውን የሚያሳይ መረጃ አለመኖር እና ለሚመለከተው የሥራ ክፍል ተደራሽ በማድረግ ረገድ ክፍተት መኖሩን መረዳት ተችሏል፡፡

የ2014 በጀት ዓመት በዘርፉ ስር በሚገኙ ተቋማት የኦዲት ግኝቶች መሰረት በተደጋጋሚ የሚነሱ የአሰራር ክፍተቶች መካከል፡- የውጭ ኦዲት ግኝቶችን የሚያመላክት መረጃ አለመኖር፣ ወቅቱን የጠበቀ የውስጥና የውጭ ኦዲት በማድረግ ረገድ ውስንነት መኖር፣ የተሟላ የኦዲት ሪፖርት አለመስጠት፣በኦዲት ሪፖርት በቀረቡ የማሻሻያ ሃሳቦች ላይ ተግባራዊ ማድረጋቸውን የሚያሳይ መረጃ አለመኖር እና ለሚመለከተው የሥራ ክፍል ተደራሽ አለመደረጉ የገንዘብ ብክነትን እንዲሁም ለብልሹ አሠራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡ በመሆኑም ዘርፉ ሊጠብቀውና ሊከላከለው የሚገባውን የመንግስት ተቋም ጥቅም የሚጎዳ ተግባር በማናቸውም ዘዴ ሊፈጸም ይችላል፡፡

4.11. የሙስና ስጋት

በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ በፋይናንስ ዘርፍ ስር የሚገኙ ተቋማት የስራ ክፍሎችና ሂደቶች መደበኛ ስራቸውን ሲያከናዉኑ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን የመለየት፣ የመከሰት ዕድላቸውን እና ቢከሰቱ ሊያስከትሉት የሚችለውን ተጽዕኖ በደረጃ (ዝቅተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ) በማለት በማስቀመጥ በመጨረሻም የሙስና ስጋት ትንተና ተካሄዷል፡፡

የስራ ክፍሎች የሙስናና ብልሹ አሰራር ስጋት ግምገማ በሶስት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን እነሱም አነስተኛ፣ መካከለኛና ከባድ በመባል ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ የግምገማ ደረጃው የሙስና የስራ ክፍሎች የመከሰት እድል በደረጃ እና ቢከሰት የሚያስከትለውን ተጽዕኖ በደረጃ ተባዝተው የሚሰጡት ውጤት ነው፡፡ በመሆኑም የግዥ አስተዳደር፣ የሙያ ብቃት ምዘና፣ የስራ ስምሪትና ፈቃድ አሰጣጥ፣ የሰው ሀብት፣ በሰው ሀብትና ልማት አስተዳደር፣ በሬጅስትራር ክፍል፣ በንብረትናጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት፣

በግዥና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት፣ የጥናትና ምርምር ቴክኖኖሎጂ ሽግግር ክፍል እና መጠጥ ቁጥጥር ትምህርት ክፍል የስራ ሂቶችና ክፍሎች ከባድ የሆነ የሙስና ስጋት ያለባቸው ሲሆን የፋይናንስ ክፍል ደግሞ አነስተኛ የሙስና ስጋት ያለባቸው መሆኑን በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል። ዝርዝር የመከሰት፣ የተጽዕኖ እና ሙስና ስጋት ደረጃውን በአባሪ ሀ ላይ ይመልከቱ።

ክፍል አምስት፡ ምክረ ሃሳቦች

- የዘርፉ ተቋማት የሚሰሩዋቸውን ስራዎች ሕጋዊነት በሕግ ክፍል ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል በዘርፉ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት ውስጥ ውጫዊ እና ውስጣዊ ውሎች ከመፈረማቸው በፊት የህግ ክፍሎች አስተያየት የሚሰጡበት አሠራር ስርዓት ስለመኖሩ መረጃዎች አያመለክትም። በመሆኑም ዘርፉ በዚህ ረገድ ያለበትን ክፍተት የማስተካከል ስራ ቢሰራ፣
- ዘርፉ የተሟላ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃጀት መኖር ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመታገል አጋዥ አደረጃጀት ነው። በመሆኑም ዘርፉ እነዚህን ክፍሎች በተሟላ መልኩ የማደራጀት ስራ ቢሰራ፣
- የዘርፉ ተቋማት ስለሚሰጡት አገልግሎት በገለልተኛ የውጭ አካል ጥናት ማስደረጋቸው ለውጤታማ አሰራር ተቀሜታው የጎላ ነው። በመሆኑም በዘርፉ ስር በሚገኙ በሁሉም ተቋማት በገለልተኛ አካል ጥናት ማድረግ ቢቻል፣
- የመንግስትና የህዝብ ሀብት በተፈለገው ጊዜና ለታለመለት ዓላማ መዋሉን በተመለከተ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ፣ አያያዝና ጥበቃ በማካሄድ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ይህ አለመደረጉ ለሙስና ሥጋት የተጋለጠ እንዲሆን ያደርገዋል። ከዚህ አኳያ በዘርፉ ተቋማት አመታዊ የንብረት ቆጠራ ከማካሄድ አንፃር ውሱንነት ያለ በመሆኑ የተሟላ የንብረት ቆጠራ ማካሄድ ቢቻል፣
- መንግስት የግዥ ስርዓት በዕቅድ እና በመርህ ደረጃ በግል ጨረታ መከናወን እንደሚገባው የግዥ ህግ በአስገዳጅ መልኩ ያስቀምጣል። በዚህ ረገድ ያለ እቅድ፤ በፐርፎርማ፣ በውስን ጨረታ እና በተደጋጋሚ ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀሙ ግዥዎች እንዳሉ መረጃዎች የሚያሳዩ በመሆኑ የዘርፉ ተቋማት በሕግ የተቀመጠውን የግልፅ ጨረታ መርህ በመከተል ግዥዎችን በዕቅድ የሚፈፀሙበት ሁኔታ ቢኖርና ግዥ የተከናወነባቸው መረጃዎችም በተደራጀ መልኩ እንዲያዙ ቢደረግ፣
- ሙስናና ብልሹ አሰራር ከሚፈፀምባቸው ጉዳዮች አንዱ በሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ በመቀጠር ባልተገባ መልኩ የመንግስት ሀብት ሲባክን እና የአገልግሎት መጓተት አንዱ ምክንያት ሲሆን ይታያል። ከዚህ አኳያ በዘርፉ ስር በሚገኙ ሁሉም ተቋማት ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ እና የስራ

ልምድ የማጣራት ስራ ስለመሰራቱ የሚገልፅ መረጃ የለለ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ እንደአንድ የትኩረት አካባቢ አድርጎ ስራውን ቢሰራ፣

- በህጉ መሰረት ሀብትና ንብረታቸውን አሳውቀው ማስመዝገብ ያለባቸው አካላት የሕግ ግዴታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ አንፃር የዘርፉ ተቋማት የተሟላ የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራ እንዳላከናወነ መረጃዎች የሚያሳዩ በመሆኑ በህጉ በተቀመጠው የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራ እንዲከናወን ቢደረግ፣
- በዘርፉ የሚገኙ ተቋማት የፕሮጀክት አስተዳደር በተመለከተ ተገቢውን መረጃ አደራጅቶ አለመያዝ፣ ግልጽ አለመሆን፣ ሙስናና ብልሹ አሠራር መከላከል የሚያስችል አሠራር አለመዘርጋታቸው ለማየት ተችሏል፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ፕሮጀክቶች ለሙስናና ብልሹ አሠራር ያለው ተጋላጭ እንዲሆኑ በር ይከፍታል፡፡ በመሆኑም ዘርፉ በዚህ ረገድ ከመቼውም ጊዜ በላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ቢችል፣
- በዘርፉ የሚገኙ ሁሉም ተቋማት በወቅቱ የውስጥና የውጭ ኦዲት በማድረግ ረገድ ውስንነት እንዳለ፣ የተሟላ የኦዲት ሪፖርት አለመስጠት፣ የቀረቡ የማሻሻያ ኃሳቦች ተግባራዊ ስለመደረጉ የሚያሳይ መረጃ አለመኖር እና ለሚመለከተው የሥራ ክፍል ተደራሽ በማድረግ ረገድ ክፍተት መኖሩን መረዳት ከመረጃዎች ማየት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ዘርፉ የሒሳብ ሠነዶቹን በትክክል መያዝ፣ ወቅታዊ የኦዲት ስራ ማከናወንና በዚሁ መሰረት የማሻሻያ ስራ ተግባራዊ ስለመደረጉ እና የሀብት ብክነት እንዳይፈጸም ለመከላከል የሚያስችል የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋቱን የማረጋገጥና ተግባር ላይ እንዲውል ቢያደርግ፣

ዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከል ስትራቴጂዎች

ሙስናን እና ብልሹ አሰራሮችን ለመቀነስ በግልጽ የተቀመጡ የሰው ኃይል ጥበቃዎችን እና ተገቢ የቁጥጥር ደረጃዎች፣ የሰራተኛ ገበያ ፖሊሲዎች በጠንካራ ትንተና ማረጋገጥ፣ ክትትል እና ቤንችማርኪንግ ማስቀመጥ፣ የቅጥር ኤጀንሲዎችን የህዝብ ተጠያቂነት ለማሳደግ የአፈጻጸም አስተዳደርን ለማስፋፋት አካታች እና ማህበራዊ ጉዳይ ላይ ያተኩሩ ንግግሮችን ማካሄድ፣ የቅሬታ ቻናሎችን ማዘጋጀት፣ የፀረ-ሙስና ባህልን ለመደገፍ የሰው ኃይል እና የአመራር ልምዶችን መጠቀም፡፡ በቅጥር ሁኔታ ላይ ግልጽ የሆኑ ድንጋጌዎች መኖር ለአሰሪዎች እና በቅጥር አገልግሎት ውስጥ ለሚሰሩ ሠራተኞች ከቅድመ ጥንቃቄ ለማምለጥ ከሚፈልጉ ሥራ ፈላጊዎች ጉቦ ለመውሰድ እድሎችን ለመቀነስ ይረዳል (OECD (2019)፡፡

ሙሰኞችንና ኪራይ ሰብሳቢዎችን በሕግ በመጠየቅ የዘረፉትን ገንዘብና ንብረት እንዲመለስ ማድረግ አንድ ስትራቴጂ ሲሆን ሙስናን ለመዋጋት ከሚወሰዱት እርምጃዎች መካከል የመጨረሻው ደረጃ እንደሆነ

በዘርፉ የሚሰሩ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ እንደሙሁራኑ ትንተና ሙሰኝነትንና ኪራይ ሰብሳቢነትን ለመዋጋት የመከላከል ተግባር ቀዳሚውን ስፍራ መያዝ ይኖርበታል፡፡ የሙስናና የኪራይ ሰብሳቢነት ወንጀል እንዳይፈጸም በእንጭጩ ለመቅጨት ዜጎች የተጠናከረ የመከላከል ዘመቻ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ሕብረተሰቡ መከላከል ላይ አተኩሮ እንዲሰራ ለማድረግ የሙሰኝነትን አስከፊ ገጽታ እንዲረዱ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ ሙሰኝነትንና ኪራይ ሰብሳቢነትን ለመዋጋት ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዘው መከላከል ነው ሲባል ወንጀሉ ከመፈጸሙና የህዝብ ሃብት ከመባከኑ በፊት የማምከን ስራ ነው፡፡

በዓለማችን በጸረ-ሙስና ትግል ቀዳሚ ተሞክሮ ያላቸው አገራት ሙስናንና ኪራይ ሰብሳቢነትን ለመዋጋት መከላከል ላይ መሰረት ያደረገ ዘመቻ ነው፡፡ ኪራይ ሰበሳቢነትንና ሙሰኝነትን ለመግታት ይቻል ዘንድ ለሙስና ተጋላጭ በሆኑ የስራ ዘርፎች የሚሰጥ ተከታታይ ስልጠና መስጠት ፋይዳው የጎላ ነው፡፡ የተጠናከረ የመከላከል ስትራቴጂ ነድፎ መንቀሳቀስ ምናልባትም ሙስናን ለማምከን ከምንጠቀምባቸው ዘዴዎች መካከል ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎንም ብልሹ አሰራሮችንና የሙስና አዝማሚያዎችን በጥናትና በምርምር በመለየት ለሚመለከተው አካል በማቅረብ አዝማሚያዎቹን የማምከን ተግባር ማከናወን የግድ ይላል፡፡

የህዝብን ገንዘብ በመዝረፍ ለመክበር የሚደረግ ሩጫን ለመግታት ቀላል የማይባል የተጠናከረና የተቀናጀ የመከላከል ሥራ መሰራት ይጠይቃል፡፡ የኢትዮጵያ ሥነ- ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን ከተቋቋማባቸው ዓላማዎች አንዱ ሙስናን መከላከል የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት ነው፡፡ ኮሚሽኑ ለሙስና ተጋላጭ በሆኑ የተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት፣ መስሪያ ቤቶችና ትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ በማተኮር ለሙስና የሚያጋልጡ አዝማሚያዎችን በማጥናትና በመመርመር የሙሰኝነት ተግባር ከመፈጸሙ በፊት ማስተካከያ እንዲደረግባቸውና ብልሹ አሰራሮች እንዲታረሙ ለማድረግ በማጥናት ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የተለያዩ አካላት እና የህብረተሰቡ ትብብርና የነቃ ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም መንግስት ከህብረተሰቡ ጋር ተባብሮ ለመሥራት የሚያስችለውን አደረጃጀትና አሠራር በመፍጠር ሕብረተሰቡ ይህንን ተገንዝቦ ተሳትፎውን የበለጠ ሊያጠናክር ይገባል፡፡

ማጣቀሻ

1. Ades, A., and R. DiTella (1997). "The new economics of corruption: A survey and some new results." Political Studies, 45: 496–515.
2. Bakare, Adewale Stephen (2011) The Crowding-Out E¤ects of Corruption in Nigeria: An Empirical Study. Journal of Business Management and Economics, 2, 59-68.
3. Blackburn, Keith, Niloy Bose and M. Emranul Haque (2011) Public Expenditure, Bureaucratic Corruption and Economic Development. Manchester School, 79, 405-28
4. Chelechele, T.I. 2009. Skills development in the South African public service: problems and solutions. Journal of Public Administration, 44(1):44–57.
5. Khan, M., Andreoni, A., Roy, P. 2016. Anti-corruption in adverse contexts: a strategic approach. SOAS Working Paper.
6. Kroukamp, H. 2002. Skills Training: A Prerequisite for the changing position and status of public servants in South Africa. Journal of Public Administration, 37(4):453–474.
7. Mafunisa, M.J. 2014. Addressing public finance management skills shortage in the South African public service. Journal of Public Administration, 49(4):1100–1112.
8. Ndikumana, Léonce (2006) Corruption and Pro-Poor Growth Outcomes: Evidence and Lessons for African Countries. Working Paper No. 120, Political Economy Research Institute.
9. OECD. 2019. Labour Market Regulation 4.0: Protecting Workers in a Changing World of Work
10. Panizza, U. (2001). "Public sector wages and bureaucratic quality: evidence from Latin America." Economía, 2: 97–151
11. Plant, K. and Padotan, R. 2017. Improving skills development in the South African public sector: an internal audit perspective. Southern African Journal of Accountability and Auditing Research, 19(1):35–48.
12. Rose-Ackerman, S. and T. Søreide. (2012). International Handbook on the Economics of Corruption, vol. 2. Cheltenham, United Kingdom: Edward Elgar Publishing.
13. Van Rijckeghem, C., and B. Weder (2001). "Corruption and the rate of temptation: Do low wages in the civil service cause corruption?" Journal of Development Economics, 65: 307–331.
14. Treisman, D. (2007). "What have we learned about the causes of corruption from ten years of cross-national empirical research?" Annual Review of Political Science, 10: 211–244.
15. An, W., and Y. Kweon (2017). "Do higher government wages induce less corruption? Cross-country panel evidence." Journal of Policy Modeling, 39: 809–826.

አባሪ ሀ፡ የስራ እና ክህሎት ዘርፍ የሙስና ስጋት ደረጃ ትንተና

ተ.ቁ	የሙስና ስጋት የሆኑ የስራ ሂደቶች	የመከሰት ዕድል	ቢከሰት የሚያመጣው ተጽዕኖ	የሙስና ስጋት	የስጋቱ መንስኤዎች	የመፍትሄ ሃሳቦች
1	ግዥ አስተዳደር	መካከለኛ	ከፍተኛ	ከባድ	ግልጽ ሆነ የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋት፣ ጥራን ያልጠበቀ ግገር፣ -ግገርን በወቅቱ ያለመፈጽም	የግልፀነትና የተጠያቂነት ሊያመጣ የሚያስችል አሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ የግዥ ፍላጎት ያቀረቡ የስራ ክፍሎች ጥራቱን አራጋግጠው እንዲቀበሉ ማድረግ፣ ግዥዎችን በሰዓቱ መፈጸም፣
2	ፋይናንስ	ዝቅተኛ	መካከለኛ	አነስተኛ	• የግልፅነትና የተጠያቂነት ስርዓት፣ የሂሳብ ሰነድ በተገቢው አለመያዝ አለመኖር	ዘመናዊ/ዲጅታል ስርዓት ስራ ላይ ማዋልጠንካራ የአሰራር ማኑዋሎችን፣ መመሪያዎችንና ደንቦችነ፣ የሂሳብ ሰነዶችን በአግባቡ መያዝ፣ በማውጣት ስራ ላይ ማዋል፣
4	የሙያ ብቃት ምዘና	መካከለኛ	ከፍተኛ	ከባድ	• ስራን በአግባቡ ሊቆጣጠሩ የሚችሉ	የኑሮ ውድነቱን ታሳቢ ያደረገ የተሻለ ደሞዝና ጥቅማጥቅምና የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት፣
5	የስራ ስምሪትና ፈቃድ አሰጣጥ	መካከለኛ	ከፍተኛ	ከባድ	• ማኑዋሎች • መመሪያዎችንና ደንቦች አለመኖር	ጠንካራ የቁጥጥርና ክትትል ስርኣት መዘርጋት፣
6	የሰው ሀብት	ከፍተኛ	ከፍተኛ	ከባድ	• ዘመናዊ/ዲጅታል አሰራር አለመዘርጋት • የተሻለ ደሞዝ/ ጥቅማጥቅምና የማበረታቻ ስርዓት አለመኖር፣ • ጠንካራ የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት አለመኖር፣የአቅም ክፍተት/ግንዛቤ ማነስ፣ የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት ማጣት	የተሻለ ግንዛቤ የሚያሲዙና የአመለካከት ለውጥ የሚያመጡ ስልጠናዎች ማዘጋጀትና ማሰልጠን፣ጥቅማጥቅም ስርኣት በመዘርጋት ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ፣
7	በሰው ሀብትና ልማት አስተዳደር	ከፍተኛ	ከፍተኛ	ከባድ	ቡድንተኝነት፣ አድሎ	መመሪያ፣ ደንቦች፣አዋጆች፣ ማኑዋሎች፣ የአሰራር ስርአት መተግበሪያ፣ ማኑዋሎች እና ሌሎች የመንግስት እና የተቋሙን ህጎችና ደንቦችን በአግባቡ

						ለመረዳት ዶክመንቶችን በክፍሉ ሰንደው ማዘጋጀትና ለአሰራር ዝግጁ ማድረግ፣
8	በሬጅስትራር ክፍል	ከፍተኛ	ከፍተኛ	ከባድ	የቁጥጥር ማነስ	ኦንላይን የሀብት ምዝገባ መጀመር፣ የሰልጣኞች አቴንዳንስ ማዘጋጀት፣ የተመዘገቡና ለስልጠና የተዘጋጁ ሰልጣኞችን ስም ዝርዝር በሴክሽን መደልደል እና ውጤት መሙያ አሰስመንት ማዘጋጀት፣ አሰልጣኞች ውጤት አደራጅተው ለክፍሉ እንዲልኩ ለማድረግ…ወዘተ) መጠቀም እና የሚመለከታቸውም አካላትና ተገልጋዮች እንዲጠቀሙ በማድረግ ከልማዳዊ አሰራር መውጣት፤
9	በንብረትናጠቅ ላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት	ከፍተኛ	ከፍተኛ	ከባድ	የቁጥጥር ማነስ	በእያዳንዱ ንብረቶች ላይ ቁጥር በመስጠት ታግ በማድረግ የመመዝገብ ስራ መስራት እና መረጃዎችን soft and hard copy ማደራጀት፣
10	በግዥና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት	ከፍተኛ	ከፍተኛ	ከባድ	ሌብነት/ብልሹ አሰራር	የፋይናንስ እና ግዥ የቴክኖሎጂ ሲስተምን (ኢፍሚስ፣ የግዥ ሲስተም) በአግባቡ ስራ ላይ በመተግበር ከልማዳዊ አሰራር መላቀቅ፤
11	የጥናትና ምርምር ቴክኖሎጂ ሽግግር ክፍል	ከፍተኛ	ከፍተኛ	ከባድ	ቡድንተኝነት	ባለሙያዎች አመዳደብ ላይ ልምድ ያላቸውን እና የሌላቸውን በማቀናጀት ሁሉን አቀፍ ተሳትፎ እንዲኖር ከሚመለከታቸው አካላት እና ስራ ክፍሎችጋር የባለሙያዎች ምደባና ድልድል ላይ በጋራ መስራት የሚያስችሉ አሰራሮችን መዘርጋት፣
12	መጠጥ ቁጥጥር ትምህርት ክፍል	ከፍተኛ	ከፍተኛ	ከባድ	ስግብግብነት	በአግባቡ መዋሉን ሾኘ አቴንዳንቶች እንዲቆጣጠሩ ማድረግ እና በፊርማ የመረካከብ ስርአት መዘርጋት፣